Selected Decisions from the Federal Supreme Court Cassation Bench (ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔወች የተመረጡ ፍርዶች)

## Case 1 (ፍርድ 1):- የሰበር መዝገብ ቁጥር 208865፣ የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች:-

1. ተፈራ ገብሩ (ዶ/ር)
2. ቀነዓ ቂጣታ
3. ፈይሳ ወርቁ
4. ደጀኔ አያንሳ
5. ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች:- ወ/ሮ እቴነሽ መለሰ - መከተ አዘናው ተወካይ -ቀርበዋል

ተጠሪ:- ማራናታ የቤት ህብረት ማህበር -አልቀረበም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 133343 ህዳር 25 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ አመልካችን ከማህበሩ ማሰናበቱ አግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደብረ ብርሃን ምድብ በመዝገብ ቁጥር 0121252 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ማጽናቱ እንዲሁም ሰበር አጣሪ ችሎት መጋቢት 8 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 1030171 የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለሰበር ለማሳረም አመልካች ሰኔ 7 ቀን 2013 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ አመልካችን ከተጠሪ ማህበር አባልነት በማሰናበት የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝ ለሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ሆኖ አመልካች በከሳሽነት ተጠሪ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የክስ አቤቱታው ይዘትም:- አመልካች ተወልደው ለ17 ዓመታት በመምህርነት ባገለገሉበት ሸዋሮቢት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ ስላልነበራቸው በመምህርነታቸው በተጠሪ ማህበር ተደራጅተው ለአምስት ዓመት የቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ እያሉ ባለቤታቸው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ባልደረባ በመሆናቸው ከጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም የትዳር አጋራቸው ወዳሉበት አዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ዝውውር ተደርጎላቸው በከተማው በማስተማር ላይ ቢሆኑም ዋና መኖሪያቸው ሸዋሮቢት ሆኖ እያለ የአማራ ክልል ባወጣው ደንብ ቁጥር 150/2000 እና መመሪያ ቁጥር 28/2009 አንድ መምህር ሲያስተምርበት ከነበረው ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ሲዛወር ከማህበር እንደሚሰናበት ባልተደነገገበት ሁኔታ እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽ አመልካችን ከማህበር አባልነት

*ለማሰናበት ስልጣን ሳይኖረው አመልካች ወደ አዲስ አበባ ከተማ ስለተዛወሩ ተጠሪን ከማህበሩ እንዲያሰናብት የፃፈለትን ደብባቤ መሰረት አድርጎ ተጠሪ አመልካችን ከማህበሩ ማሰናበቱን የገለፀለት መሆኑን በመግለጽ መደበኛ ነዋሪነቷ ሸዋሮቢት ሆኖ እያለ እና በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ እንዳልሆነች በማስረጃ ተረጋግጦ ባለቤት ተጠሪ አመልካች ከማህበር እንድትሰናበት መወሰኑ አላግባብ ስለሆነ ውሳኔው ተሰርዞ አመልካች ወደ ማህበሩ እንድትመለስ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡*

*ተጠሪም በመልሱ፡- አመልካች የማህበሩን የስራ ክልል ለቃ ስለሄደች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) መሰረት ከማህበሩ እንድትሰናበት የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዳሳወቃቸው ለአመልካች በማሳወቅ ከ23 ማህበሩ አባላት አራቱ ብቻ ባልተገኙበት ምልዐት ጉባኤ ተሟልቶ አመልካች ከማህበሩ እንድትሰናበት የተለለፈ ውሳኔ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሆኖ ተጠሪ ከማህበሩ እንድትሰናበት ያስተላለፈው ውሳኔ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲጠና ጠይቀዋል፡፡ የስር 2ኛ ተከሳሽም አመልካችን ከማህበር ስላላሰናበቱ የቀረበበት ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተቃውሞ በፍሬ ነገር ላይም መልስ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም በስር 2ኛ ተከሳሽ የተነሳውን መቃወሚያ በመቀበል ከክርክሩ አሰናብቶ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራና ቀኙን አከራክሮ እና የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ አባላት ከማህበሩ የሚሰናበቱበት ምክንያት በአዋጁ የተሻረ ሲሆን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) ሥር የተቀመጠው አንድ አባል የማህበሩን የስራ ክልል ለቆ ከሄደ ከማህበሩ ይሰናበታል በማለት የሚደነግግ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 64(2) ስር ማንኛውም ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ፣መመሪያ እና የተለምዶ አሰራር በአዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው የደነገገ በመሆኑ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) ሥር የተመለከተውን አዋጁን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይገባ ሲሆን መተዳደሪያ ደንቡ አዋጁን አይቃረንም ቢባል እንኳን አመልካች የምትተዳደርበት ንብረቷ መኖሪያዋ እና ማህበራዊ ህይወቷ ያለው ሸዋሮቢት ከተማ በመሆኑ በዝውውር ምክንያት የስራ ቦታዋ አዲስ አበባ ቢሆንም እየተመላለሰች የምትሰራ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ እንዲሁም አመልካች ከማህበሩ እንድትሰናበት የተያዘው ቃለ ጉባኤ አባላት ሳይሰባሰቡ በአንድ ሰው ብቻ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ በጉዳዩ ላይ አባላት የሰጡትን ሃሳብ ያላካተተ በመሆኑ አመልካች ከማህበሩ መሰናበቷ አግባብ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡*

*ጉዳዩን ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመምህራን መሆሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 150/2009 ተፈፃሚነት ወሰኑ በክልሉ በመንግስት ትምህርት ቤቶች በማስተማር ስራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ መምህራን ብቻ ሆኖ የደንቡ መሰረታዊ አላማም በመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የመምህራን ፍላጎት በመቀነስ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ መሆኑን መረዳት የሚችል ሲሆን አመልካች አዲስ አበባ ከተማ ተዛውራ የምትሰራ መሆኑን በራሷ ምስክሮች ጭምር የተረጋገጠ መሆኑን፣ በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ*

ለማድረግ በወጣው የህግ ማዕቀፍ መሰረት ለመጠቀም የምታቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ሆኖ ተጠሪ አመልካችን ከማህበሩ ያሰናበተበት አግባብ የማህበሩን ህግ ደንብ እና ሌሎች ህጎችን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር ስንብቱ ህገ ወጥ ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሻረ ሲሆን፣ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች በመምህርነት ከሸዋሮቢት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ዝውውር የተደረገላት መሆኑ የታመነ ፍሬ ነገር በመሆኑ መምህርነት የሙሉ ጊዜ ስራ በመሆኑ ምንም እንኳን የአመልካች ምስክሮች ሸዋሮቢት ከተማ ለቃ እንዳልሄደች እና እንደምትመላለስ የገለጹ ቢሆንም ከቦታ እርቀት አንፃር እና አመልካች ወደ አዲስ አበባ ለመዛወር ከጠየቀችበት ምክንያት አንፃር አሳማኝ ባለመሆኑ እና የፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 185 ድንጋጌን ሊያስነሳ የሚችል አጠራጣሪ የመስሪያ ስፍራ ስለሌለ በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 183 ድንጋጌ መሰረት የጉዳዮቿ እና ጥቅሞቿ ዋና ስፍራ የሙሉ ጊዜ ስራዋን የምትሰራበት አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን ተጠሪ የስራ ክልል የለቀቀች በመሆኑ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 9(2) እና 14(4) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ግዴታዋን ባለመወጣቷ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀና ሲሆን የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎቱም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሰርዞታል።

አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በሰበር ለማሳረም ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፦ አመልካች በሳምንት አልያም በአስራ አምስት ቀን የምትመላለስ መሆኑ ማህበራዊ ህይወቷ ዕድሯ እና የቤት ንብረቷ በሸዋሮቢት ከተማ እንደሚገኝ ከአዲስ አበባ ከተማ የቤት ተጠቃሚ ያለመሆኗ ተረጋግጦ እያለ የፍትሐብሔር ህጉን ቁጥር 185 ድንጋጌ በሚፃረር መልኩ የስራ ዝውውር በማድረግ ብቻ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20፣32 እና 41 በሚቃረን መልኩ፣ መደበኛ መኖሪያዋን እንደቀየረች መቆጠሩ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ያልፀደቀ ረቂቅ ሆኖ ተፈፃሚነት የሌለው ከመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ስር ከተደነገገው ውጭ አንድ አባል የማህበሩን የስራ ክልል ለቆ ከሄደ እንደሚሰናበት ተጨማሪ መስፈርት መደንገጉ አዋጁን የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚነት የሌለው ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ማድረጋቸው፣ አመልካች በመምህርነት ሳይሆን እንደማንኛውም ነዋሪ ቦታ ለማግኘት ተደራጅታ ሁሉን ነገር ብታሟላም መንግስት በጊዜ ቦታውን ባለማቅረቡ ምክንያት የቤት መስሪያ ቦታ ሳታገኙ የስራ ዝውውር በማድረግ ተወልዳ አድጋ ለ17 አመት በመምህርነት ባገለገለችበት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ እንዳታገኝ ከተጠሪ ማህበር መሰናበቷ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ ወደ ማህበሩ እንድትመለስ እንዲወሰን አመልክተዋል። የሰበር አጣሪ ችሎቱ አመልካች በስራ ዝውውር እንጅ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸውን ያልቀየሩ መሆኑን፣ ማህበራዊ ኑሮአቸው ሸዋሮቢት ከተማ መሆኑን የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት በሰነድ እና በሰው ማስረጃ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩን

*በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች አመልካች ከማህበሩ ሊሰናበቱ ይገባል ያሉበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 220/2007 አላማ አንፃር መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- አመልካች በቋሚነት በዝውውር አዲስ አበባ ከተማ በመምህርነት እየሰራች ለመሆኑ በአቤቱታዋ ጭምር አረጋግጣ ባለችበት ሁኔታ አድራሻየ ሸዋሮቢት ነው የሚለው መከራከሪያ አግባብነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር የመንግስት ሰራተኞች ስራቸውን የሚከናውኑበት ቦታ አንድ መኖሪያ እንደሚኖራቸው የሚደነግገውን የፍትሐብሔር ህጉን ቁጥር 179 የሚቃረን ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ የማህበሩ የስራ ክልል ሸዋሮቢት ከተማን ለቃ በዝውውር አዲስ አበባ ከተማ በቋሚነት እየሰራች በመሆኑ በማህበሩ ደንብ መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከአባልነት መሰናበቷ ህጋዊ ሆኖ እያለ አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን አባላት በበቂ ምክንያት ከማህበር ሊሰናበቱ እንደሚችሉ በአዋጁ የተቀመጠ ሲሆን ለማሰናበት የሚያበቁት ምክንያቶች ደግሞ በማህበሩ ደንብ ላይ በግልጽ በመቀመጣቸው በአዋጅ ቁጥር 220/2007 አንቀጽ 18 መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ሲያሰናብት የሰሩትን ጥፋት በዝርዝር ማስቀመጡ አስፈላጊ በመሆኑ አመልካች በጠቅላላ አባላት በፀደቀው ደንብ መሰረት በበቂ ምክንያት ከማህበሩ ተሰናብታ እያለ የማህበሩ ደንብ ቁጥር 14(4) ድንጋጌ የአዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ድንጋጌን እንደሚቃረን የቀረበው መከራከሪያ የአዋጁንና የደንቡን ዓላማ ከግምት ያስገባ አለመሆኑን፣ አመልካች ከአማራ ክልል ውጭ በመምህርነት እየሰራች የደንብ ቁጥር 150/2009 ቁጥር 3 እና 4 ድንጋጌን በሚቃረን መልኩ ወደ ማህበር አባልነት ለመመለስ የምታቀርበው አቤቱታ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ እና አግባብ ባለው ባለስልጣን ተመዝግቦ ለማህበሩ ህጋዊ ሰርተፍኬት ተሰጥቶ ባለበት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ነው በማለት አመልካች የምታቀርበው መከራከሪያ ተገቢ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚዎች የስር ፍርድ ቤቶች የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻራቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ለሰበር ቅሬታው መሰረት የሆነው ውሳኔ ፀንቶ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡*

*የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ አመልካች ለ17 አመታት በመምህርነት ባገለገሉበት ሸዋሮቢት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ ስላልነበራቸው የአማራ ክልል ባወጣው ደንብ ቁጥር 150/2000 እና መመሪያ ቁጥር 28/2009 መሰረት አድርጎ በተጠሪ ማህበር ተደራጅተው ለአምስት አመት የቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ እያሉ ባለቤታቸው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ባልደረባ በመሆናቸው የትዳር አጋራቸው ወዳሉበት አዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም ዝውውር ተደርጎላቸው በከተማው በማስተማር ላይ ቢሆኑም መደበኛ መኖሪያቸው ሸዋሮቢት ከተማ ሆኖ እያለ እና በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪ ቤት ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪን የስር 2ኛ ተከሳሽ ከማህበሩ እንዲያሰናብት የፃፈለትን ደብዳቤ መሰረት አድርጎ ተጠሪ*

አመልካችን ከማህበሩ ማሰናበቱን አግባብ ባለመሆኑ ውሳኔው ተሰርዞ ወደ ማህበር አባልነታቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ላቀረቡት ክስ ተጠሪ በሰጠው ምላሽ የስራ ክልል ለቃ ስለሄደች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) መሰረት ከማህበሩ እንድትሰናበት የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዳሳወቃቸው ለአመልካች በመግለጽ ምልዐተ ጉባኤ ተሟልቶ አመልካች ከማህበሩ እንድትሰናበት የተሳለፈ ውሳኔ እንደሆነ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ማህበር የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታን ለማግኘት የተደራጁት በመምህርነት ባገኙት ልዩ መብት መሆን አለመሆኑ? በመምህርነት ያገኙት ልዩ መብት ነው ከተባለ በመምህርነት ሙያቸው የትዳር አጋራቸው ወደ አለበት አዲስ አበባ ከተማ ዝውውር በማግኘታቸው ለመምህራን የተሰጠውን ልዩ መብት ያላግባብ ተጠቅመዋል ተብሎ ከማህበር አባልነታቸው ሊሰረዙ ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች ለጉዳዩ ተገቢነት ካለው ህግ አንፃር ማየት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የመምህርነት ሙያ ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት የሚጫወተው ቁልፍ ሚና ለማሳካት የበኩሉን ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ መምህራን የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ግዴታቸውን በተነቃቃ መንፈስ መወጣት እንዲችሉ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት በሙያው ብቃት ያላቸው መምህራን ፍልሰት ለመቀነስ የመኖሪያ አካባቢን በማመቻቸት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን በማቃለል ቤተሰቦቻቸው እና መላው ህብረተሰቡ ለሙያው አወንታዊ አመለካከት ኖሯቸው የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ የህግ ማዕቀፍ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ታምኖበት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመምህራን መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ለማስፈፀም ደንብ ቁጥር 150/2009 የወጣ መሆኑን ደንቡ ያመለክታል፡፡ እነዚህ ለመምህራን የሚደረጉት በሚያስተምሩት አካባቢ በመንግስት ወይንም በህዝብ ተሳትፎ የሚሰሩ ቤቶች በነፃ ወይም በተመጣጣኝ ኪራይ ማግኘት በሚያስተምሩበት ቦታ ወይንም አካባቢ በሚገኝ ቀበሌ እና ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ እንደማንኛውም ዜጋ በማህበር ተደራጅተው በህጉ የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ የቤት መስሪያ ቦታን ከአነስተኛ፣መካከለኛ እና ሜትሮፖሊያን ከተሞች ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ከደንቡ ቁጥር 6 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ መምህራን በሚሰሩበት ወረዳ ውስጥ ካሉት ከተሞች መካከል በመረጡት ከተማ ቤት የመስራት ፍላጎት ኖሯቸው መመሪያ ቁጥር 28/2009 በሚፈቅደው መሰረት እንደማንኛውም ዜጋ 14 እና ከዚያ በላይ ሆነው በማህበር ተደራጅተውና ከቤት መስሪያ ዋጋው 20 በመቶ መቆጠባቸውን አረጋግጦ ቦታ መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ቁጥር 6(4) ያመለክታል፣ ደንብ ቁጥር 150/2009 መምህራን ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በተለየ ያስቀመጠው ነገር ቢኖር በከተማ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ከሚዘጋጀው ቦታ ውስጥ 20-30 በመቶ የሚሆነው ለመምህራን ቅድሚያ ተሰጥቶ የሚመደብ መሆኑን ከቁጥር 6()፣7(5) እና 9(5) ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ መምህራን እንደ ማንኛውም ዜጋ በመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው የከተማ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታን ከሚያገኙ በቀር በመምህርነታቸው የተለየ መብት ተሰጥቷቸዋል ብሎ ለመናገር ብዙም የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የተለየ መብት ተሰጥቷቸዋል ቢባል እንኳን በመጀመሪያ ደንቡ የወጣበት

ዓላማ መነሻ ያደረገው የአማራን ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትን ቢሆንም ጥራት ያለው ትምህርት ለዜጎች ማዳረስ እንደ ሀገር መብቱን ከዓላማው ውጭ ተጠቅሞበታል የሚያስብል አይሆንም፡፡ ሁለተኛ አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 33(2) በዜግነታቸው ህግ የሚያስገኘውን መብት ጥበቃ እና ጥቅም የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ በአንቀጽ 41(1) እና 32(1) መሰረት እንደቅደም ተከተላቸው በመረጡት የመምህርነት ሙያ መሰማራት እና በመረጡት የሀገሪቱ አካባቢ የመኖር መብታቸውን ማንኛውም የመንግስት አካል የማክበርና የማስከበት ሀላፊነት እና ግዴታ ያለበት መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) ይደነግጋል፡፡ አመልካች ባለትዳር መሆናቸውን እና የባለቤታቸው ስራ ቦታ አዲስ አበባ መሆኑ ግራቀኙን ያላከራከረ ሲሆን ባልና ሚስት አብሮ ለመኖር የሚገደዱ መሆኑና ተለያይተው መኖር የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 64(1) እና 66(1) ያስነዝባል፡፡ አመልካችን ከትዳር አጋራቸው ለማገናኘት ሲባል ዝውውር መደረጉ በቤተሰብ ሕጉም ሆነ በሲቪል ሰርቢስ ህጉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ እያለ አመልካች በመምህርነታቸው ከአዲስ አበባ ከተማ የቤት ተጠቃሚ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ፣አመልካች በደንብ ቁጥር 150/2009 ቁጥር 10 መሰረት በራሳቸውም ሆነ በትዳር አጋራቸው ስም አስቀድሞ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት መይንም ቦታ ያላቸው መሆኑ ክርክር እና ማስረጃ ባልቀረበበት፣ እንዲሁም ቦታ ለማግኘት የተደራጀ ሰው በስራ ወደ ሌላ ቦታ በመዛወሩ ምክንያት ከመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር አባልነቱ ይሰረዛል የሚል በአዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ሥር ባልተደነገገበት የአለምካች ከማህበር አባልነት መሰረዝ ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ በአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ከ14 በታች በሆነ ጊዜ በተናጠል በሊዝ መነሻ ዋጋ የቤት መስሪያ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ (ደንብ ቁጥር 7(3)፣8(3)፣ 9(3) ድንጋጌን ይመለከቷል) ስለዚህ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ማግኘት መብት በማህበር በመደራጀት የሚገኝ ሳይሆን ከህግ የሚመነጭ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 220/2007 የመደራጀት አላማው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን በጋራ ጥረት በመቋቋምና በማስወገድ በግል ቢሰራ የሚደርሰውን ጉዳት እና ኪሳራ በመከላከል የእያንዳንዱን ጉዳት እና ኪሳራ በመቀነስ የአባልነቱን ጥቅም ማስከበር መሆኑን ከቁጥር 4(4) እና 4(6) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አባላት ከማህበሩ የሚወጡበትና የሚመለሱበትን ሁኔታ የሚያካትት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 14(2) () ስር የተደነገገ ቢሆንም ድንጋጌው መታየት ያለበት ከአባልነት መብት እና ግዴታቸውን ከመወጣት አንጻር እንጅ የአባልነቱን ጥቅም በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ የተቋቋመ ማህበር በህጉ ያልተቀመጠውን መስፈርት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በማስፈር አባልነቱን ባልተገባ ምክንያት ከማህበር በማሰናበት በህግ የሚያገኙትን መብት ማሳጣት በማህበር የመደራጀት ዓላማ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች በመምህርነታቸው የቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በተጠሪ ማህበር ተደራጅተው በመጠባበቅ ላይ እያሉ በመምህርነት ሙያቸው የትዳር አጋራቸው ወደሚሰሩበት አዲስ አበባ ከተማ በመዛወራቸው ምክንያት ከተጠሪ ማህበር መሰናበታቸው ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 103071 መጋቢት 8 ቀን 2013 ዓ፣ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ደብረ ብርሀን ምድብ በመዝገብ ቁጥር 0121252 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሁም የሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 013343 ህዳር 25 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቀጥር 17584 ሐምሌ 14 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

3. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ።

4. ውሳኔው መጋቢት 5 ቀን 2014 ዓ፣ም በችሎት ተነቧል። መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

## Case 2 (ፍርድ 2)፡- የሰበር መዝገብ ቁጥር 181649፣መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-

1. ተፈራ ገብሩ (ዶ/ር)
2. ተነዓ ቂጣታ
3. ፈይሳ ወርቁ
4. ደጀኔ አያንሳ
5. ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ደጋረገ ሙሉ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ውብናት ላቀ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር የተጀመረው በአማራ ክልል በሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የስር ተጠሪ፣የአሁን ተጠሪ የስር አመልካች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር በወረዳው ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ከአሁን አመልካች ጋር ያለን ጋብቻ እንዲፈርስ በጋራ ያፈራናቸው ንብረቶች እንድንካፈል በማለት ዘርዝራ በማቅረብ እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ባቀረቡት መልስ ተጠሪዋ ባቀረበችው የንብረት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ክርክር ያቀረበ ሲሆን በራሱ በኩል ባቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከተጠሪ ጋር ልንካፈል ይገባል የሚላቸውን ንብረቶች በመዘርዘር በመጠየቅ፣ የሰራተኛ ዕዳ አራት ኩንታል በቆሎ አንድ ኩንታል ዳጉሳ፣ አንድ ኩንታል ጓያ አለብን ልንከፍል ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ መልስ ያቀረበት ሲሆን፣ የሰራተኛ የጋራ ዕዳ አለብን በማለት የቀረበው ሐሰት ነው፡፡ ይህ ተቀጠረ የተባለው ልጅ የአሁን አመልካች የግል ልጅ ነው የኔም ሶስት ልጆች የግል ነበረኝ የግል ከብቶች ነበራቸው እነዚህ ልጆች አብረው ከእኛ ጋር ያደጉ ሲሆን ለሰሩበት ልንከፍላቸው አልተስማማንም አልቀጠርናቸውም፡ የአሁን አመልካች ልጅ እንደልጅ ከቤት ነበረ እንጅ የተቀጠረ አይደለም፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤት የሰው ምስክሮች በመስማት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት የጋራ ዕዳ በማለት ያቀረበው የሰራተኛው ዕዳ 6 (ስድስት)

*ማዳበሪያ እህል በጋራ ሊከፍሉ ይገባል፣ የባልና ሚስት ንብረቶች ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል። የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ የባልና ሚስት ንብረት በተመለከተ በተወሰኑ ንብረቶች ላይ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሜ አጣርቶ እንዲወስን የመለሰ ሲሆን፣ የሰራተኛ ዕዳ የተባለውን የስር ውሳኔ በማፅት ወስኗል።*

*የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ለአራሽ ሰራተኛ አበል የተባለውን 6 (ስድስት) ማዳበሪያ እህልን በተመለከተ የእርሻ ስራ ሰራሁ የሚለው ግርማው ደጋረገ የተባለው ሰው ቀርቦ ሳይጠየቅ የአሁን አመልካች መብት የለውም እና ስለ ግርማው ደጋረገ ውክልና ባልያዘበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ ለአራሽ አበል ከሆነው 6 (ስድስት) ማዳበሪያ እህል ውስጥ ዕዳ በመሆን ድርሻዋን ትክፈል በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የአሁን ተጠሪ ይህን ዕዳ ልትከፍል አይገባም። የጋራ ንብረቶችን በተመለከተ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ በመስጠት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻሻል ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው።*

*የአሁን አመልካች በ06/10/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤት የሰራተኛ ደመወዝ 6 ማዳበሪያ ሰብል ዕዳ የአለብን ስለመሆኑ በግራ ቀኝ ምስክሮቻችን ተጣርቶና ተረጋግጦ እያለ ተጠሪም ይህን አምናበት የሰራተኛ ደመወዝ ሰብሉን የከፈለች ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቱ ግን የሰራተኛ ደመወዝን እዳ ያለብንን ባለገንዘቡ ከሶ ይጠይቅ በማለት ለሌላ ወጭ በሚዳርግ መልኩ በምስክሮቻችን የተረጋገገውን እዳ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻሻልልኝ በማለጽ በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ቅሬታውን አቅርበዋል።*

*የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት የስር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ለእርሻ ሰራተኛ የተከፈለ እዳን በድርሻዋ ለአመልካች ልከፍላት አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንድትሰጥ ባዘዘው መሰረት በ06/2/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሰራተኛ ደመወዝ የተባለውን በድርሻዋ ለአሁን አመልካች መክፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢና ሕጋዊ ስለሆነ እንዲፀናልኝ በማለት በዝርዝር ክርክሯን አቅርባለች። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።*

*የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል።*

*በባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር ወቅት ባለመብቱ ቀርቦ ባልጠየቀበት ሁኔታ ባል ወይም ሚስት የሌላ ሰዉ እዳ ስላለብን በክፍፍል ሂደቱ ታሳቢ ይደረግ የሚል ክርክር ማቅረብ የማይገባ ስለመሆኑ*

*እንደመረመርነው የአሁን አመልካች የእርሻ ስራን ለሰራልን ለአቶ ግርማው ደጋረገ ሊከፈል የሚገባው ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ልትከፍ ይገባል በማለት ዳኝነት ለመጠበቅ መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ አቶ ግርማው ደጋረገ የአሁን አመልካች ልጅ መሆኑን ከግራ ቀኝ እና ከስር ፍ/ቤት የውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አቶ ግርማው ደጋረገ በግራ ቀኙ ተቀጥረው የእርሻ ስራ የሰራላቸው ከሆነ እና ሊከፍሉት የሚገባው የስራ ዋጋ ወይም ደመወዝ ካለና መብት አለኝ የሚል ከሆነ አግባብነት ባለው የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፣በህግ አግባብ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ አቀርቦ ከመጠየቅ የሚከለክለው ነገር አልነበረም፡፡ የአሁን አመልካች ግን ይህን ግለሰብ ወክለው በዚህ ጉዳይ ዳኝነት የመጠየቅና እንዲወሰንልኝ ብሎ ለመጠየቅ በሕግ አግባብ የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ከሳሽ ለክስ ምክንያት በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ነገር ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ለመጠየቅ እንደማይፈቀድለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ የተያዘው ጉዳይ ሲታይ የአሁን አመልካች አቶ ግርማው ደጋረገ የእርሻ ስራ ስለሰራልን በዚህ ምክንያት ልንከፍለው የሚገባውን ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን እንድትከፈል በማለት ስለ ግርማው ደጋረገ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ጠይቆ እንዲወሰንለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ለሰራተኛ የሚከፈል እዳ ቢኖር እንኳን የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ለገንዘብ ጠያቂው እንጅ ለአመልካች የምትከፍልበት አግባብ የለም፣ የስር ወረዳው ፍ/ቤት እና የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በዚህ ጉዳይ መብትና ጥቅም የለውም ብሎ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው የሰጡት ውሳኔ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር የአሁን አመልካች ስለ ግርማው ደጋረገ ዳኝነት እንዲወሰንለት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም የለውም በማለት በማረም የሰጠው ውሳኔ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡*

*ሲጠቃለል የስር የክልል ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልክች በእርሻ ስራ ተቀጥሮ አገልግሏል በማለት የጠቀሰውን አቶ ግርማው ደጋረገ መብት በተመለከተ ይህ ግለሰብ ራሱ ሳይጠይቅ ስድስት ማዳበሪያ እህል እዳ አለብን ከዚህ ውስጥ ተጠሪ ድርሻዋን ለአመልካች ልትከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ የሚከተለው ተወስኗል፡፡*

*<u>ውሳኔ</u>*

1. *የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡*

2. *የዚህ ወሳኔ ግልባጭ በስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።*
3. *ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ።*
4. *ይህ ችሎት በ27/12/2011 ዓ.ም የሰጠውን አፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚሁ ውሳኔ ተነስቷል። ይፃፍ። መዝገቡ ተዘግቷል።*